# የቴዲ እንባ

ከሠረቀ ብርሃን
ሐምሌ 2000

*... ፍቅር አጥተን እንጂ በራብ የተቀጣን*
*አገሩ ገራ ገር ምድሩ መች አሳጣን...*
*«ቴዲ - ጃህ ያስተሰርያል»*

ለሃገራችን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አካባቢያዊ ችግሮች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦችን ለዛ ካላቸው ጣዕመ ዜማዎች ጋር አቀናብሮ፣ ለሕብረተሰብ ጠቃሚና ሥነ ልቦና አነቃቂ መልክቶችን በማስተላለፍ ተደናቂነትን ያተረፈው ቴዲ አፍሮ የተናገረውን ለሰማ፣ የዘፈናቸውን ዘፈኖች ግጥም ባንክሮ ላዳመጠ፣ መልእክቶቹ ያዘሉት ቁም ነገር ባጭሩ፤ እንተባበር፣ እንተሳሰብ፣ ከወሬ ይልቅ ሥራን እናስቀድም፣ ይቅር መባባልን እንወቅ፣ ለሰላም እድል እንስጣት የሚል ነው:: የቂም በቀል አገዛዝ አያዛልቀንም፣ ኢትዮጵያዊነት እንጂ ጎሰኝነት ይከፋፍለናል እንጂ አያሳድገንም፣ ሕዝብን መናቅ አያዋጣንም፣ ብንተባበር ሃገራችንን ከተዘፈቀችበት ድህነት፣ ረሃብና በሽታ ማላቀቅ እንችላለን፤ ለሃገራችን እድገት የሚያስፈልገውን ሁሉ ተፈጥሮ ባርኮ ሰጥቶናል፣ የጎደለን ይቻላል የሚለው የሕብረትና የወንድማማችነት ስሜት ብቻ ነው በማለት ሙያዊ ግዴታው ከሚጠይቀው በላይ ኢትዮጵያዊነቱን በአፍ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ያረጋገጠ ልበ-ቅን ወጣት ነው::

ለሃገር አለኝታ፣ ለወጣቱ ትውልድ ዓርዓያ ይሆናሉ ተብለው ተስፋ የተጣለባቸው ሽማግሌዎቻችን ቅሌታቸው እየበዛ ወኔና ብልሃት እየሸሻቸው በሄደበት ዘመን የኢትዮጵያን ትንሳኤ ለማብሰር ብቅ ያለ ያዲሱ ትውልድ በጎ ጎን መገለጫ::  ታዲያ ኢትዮጵያዊነትን ከሁሉ በላይ በማስቀደሙ የተበሳጨው፤ ቅናት፣ እብሪትና ምቀኝነት እንደቅሪላ የወጠረው ስልጣን ላይ ያለው የወሮበሎች ቡድን ምክንያት ፈጥሮ፣ በሃሰት ወንጅሎ፣ የተመቸውን ሕግ ጠቅሶ ለእስር ዳረገው:: መንፈሱን ለማላሸቅ፣ ምኞቱን ለመቅጨት፣ የራዕዩ ጮራ ለሌሎች እንዳይፈነጥቅ ለመጋረድ የታቀደ ተራ የቂም በቀል፣ የጥጋብና የማንአለብኝነት እርምጃ ተወሰደበት:: ንፁህ ኢትዮጵያውያን ከልብ ስናዝን ሆዳሞችና አገር አጥፊዎች ደግሞ ፍትህ ላምባገነንነት ቦታውን በለቀቀበት አገር የሕግ የበላይነት መከበር አለበት እያሉ ተመጻደቁብን::

የሚያሳዝነው የሙያ ባልደረቦቹም ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን፣ ከጥቂት አድናቂዎቹ በስተቀር፣ ከንፈር ከመምጠጥና የሃዘን ስሜት ከማሳየት የዘለለ ለቁም ነገር የሚበቃ እርምጃ ለመውሰድ ችላ ማለታቸው ነው:: የፍትሕ ደብዛው በጠፋበት በወሮበሎቹ ፍርድ ቤት የቴዲ ጉዳይ ፍትሃዊ እልባት ያገኛል ብለን እናምናለን በማለት ራሳቸውንና ሌሎችን የሚያታልሉ እንደ የሰሜን አሜሪካ ስፖርት ፌዴሬሽን የመሳሰሉትና ሌሎች ድርጅቶች ዜጋዊ መብቱና ኢትዮጵያዊነቱ ሲደፈር በግልጽ እያዩ የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ከመቅለስለስ ሌላ የወሰዱት አቋም የለም:: ሲመቻቸው ሊጠቀሙበት እንጂ ሲቸገርና በሃሰት ሲወነጀል ዞር ብለው ለማየት፣ ጠንከር ብለው ለምን ይህ ይደረጋል፣ አይገባም ለማለት አድር ባዮች ናቸውና ወኔ አነሳቸው፣ ሆዳቸው በለጠባቸው:: ውሻ በበላበት የጮሃል ነውና!

ለሃገራቸው የሚያስቡ፣ የሚናገሩትን በሥራና በተግባር የሚተረጉሙ፣ የሕዝብ ሽክም ከመሆን ይልቅ መከታ ለመሆን የመንፈስ ጥንካሬው፣ ብቃቱና ችሎታው ያላቸው ሰዎች ብቅ ሲሉ ጭንቅላታቸውን እየኮረኮሙ ተስፋ ማስቆረጥ የዚህ የወሮበሎች ቡድን የተለመደ መሰሪ ዘዴ መሆኑ ግልፅ ስለሆነ ሊያስገርመን አይገባም:: ሊያስገርመንና ሊያሳዝነን የሚገባው አይናችን እያየ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ህልውናቸውና መብታቸው ሲገፈፍ፣ ሃገራችን ስትበደል እንደ ቴዲ አይነት አስተዋይ ሰዎች ችግሩ እንዲታረም ጥረት በማድረጋቸውና የተሻለውን መንገድ በሰላማዊ መንገድ በመጠቆማቸው ሲጠቁ፣ የሕዝብን ፍላጎት ስላንፀባረቁ ለበደል መዳረግ አይገባቸውም በማለት ከጥቃት ለማዳን ሙከራ እንኳን ለማድረግ ትብብር አለመኖሩ ነው::

ቴዲ ለሃገሩ ስለተቆረቆረ፣ የተሻለ አቅጣጫ ስለጠቆመ፣ የወገኖቹ ጥቃት ስለተሰማው በፍትህ ስም እንዲማቅቅ ተደረገ:: እንደሌሎቹ፣ በስራና በተግባር ሳይሆን በወሬ ብቻ አገሬ አገሬ ከሚሉት ያገር ሽክሞችና ሆድ አደሮች ለየት ባለና በቅርብ ታሪካችን (የቀን ጅቦች በበዙበት ዘመን) ባልተለመደ መልኩ ሕሊናዬን ለጥቅም ስል አላስቀፈድድም፣ ጥፋት እያየሁ አላየሁም ብዬ ራሴን ለድሎት አላታልልም፣ ያገሬን ሕዝብ በደል እየሰማሁ አልሰማሁም በማለት ሆዴን ለመጥቀም መስሎ መኖርን አልመርጥም፣ ሙያዊና ሃገራዊ ግዴታዬን የለማንም ተፅእኖ የመፈጸም መብቴን አላስነካም ስላለ በሀሰት ተወነጀለ፣ እስር ቤት ተወረወረ፣ ተጉላላ፣ ተሰቃየ:: ሁለተኛ አይለምደኝም ብሎ ተስፋ እንዲቆርጥ፣ ብቻውን ያለደጋፊና ያለአሳቢ የቀረ እንዲመስለው የሚያደርግ የስነ ልቦና ሰቆቃ

ተፈጸመበት:: ወሮበሎቹ እብሪታቸው አይን እያወጣ ሄዶ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አንገት ያስደፉበትን ዘዴ በግልጽ ቴዲም ላይ ደገሙት:: በለሰለሰ አንደበት አብሪታቸውን ለማንበረክክ የሚችለውን የቴዲን የሰላም ሃይልና የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ መቋቋም እንደማይችሉ ስለገባቸው እንደ ጦር ፈሩት:: ባዶ እጁን የሰላማዊነትን መንፈስ ታጥቆ የሕዝብን ፍላጎት ስላንጸባረቀ ወኔውን በማያዳግም ሁኔታ የሚያላሽቅ ዘዴ ፈልገው እያጉላሉ ሊጫወቱበት ዶለቱ:: ሆዳም ቡችሎቻቸውን በያቅጣጫው አሰማርተው ቴዲን ተስፋ የማስቆረጥ ዘመቻቸውን ተያያዙት::

ሆኖም የፈለጉትን ያለምንም ይሉኝታ በእብሪት ለመፈፀም ቢችሉም ሃገሪቱን አሁንም የቆራጥ ልጆች ድሃ የማድረግ አላማቸው አልተሳካላቸውም:: ለሆዳቸው አድረው ወገኖቻቸውን ለከፋ ጥቃት የሚያጋልጡ እንክፎች የበዙትን ያህል፣ ቆራጥ፣ ባላማቸው የጸኑና በቀላሉ የማይበገሩ ልጆችም ሃገራችን እያፈራች እንደሆነ ቴዲ አንዱ ማስረጃችን ነው::

ግንባርና ልብ ላይ እያነጣጠሩ ሕዝብ የፈጁና ያስፈጁ አረመኔዎች ያለምንም ሃፍረት ደረታቸውን ወጥረው፣ ልባቸውን አሳብጠው በሚርመሰመሱባት አገር፣ ቴዲ እውነት ስለተናገረና ለሃገሩ ስለተቆረቆረ አንገቱን ደፍቶ እንዲያዝንና እንዲያለቅስ፣ ፍትህ አጥቶ እንዲማቅቅ ተደረገ:: ከጥፋታችሁ ተማሩ፣ ለራሳችሁ/ለጎሳችሁ ብቻ ሳይሆን ለሃገራችሁ አስቡ፣ ይቅር ባይነትን ተቀበሉ ስላለ እንደጥፋት ተቆጥሮበት ምክንያት እየተደረደረ እንዲጉላላ ተገደደ:: የሕዝብን መብት ረግጠው ስልጣንን በጉልበት የቀሙ ጉዶች ያለገደብ በሚንደላቀቁባት አገር ቴዲ እንደተራ ወንጀለኛ ውድ ጊዜውን ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ለማዋል የሚያስችል ተሰጥዖውን እንዳይጠቀምበት፣ ብሩህ አእምሮውን ለቁም ነገር እንዳያውል በእስር ቤት እንዲንገላታ በሆዳም ዳኞች የፍርደ ገምድል እርምጃ ተወሰደበት::

ቴዲ የታሰረበት እስር ቤት መግባት የሚገባቸው ሀገርን ለሽያጭ ያቀረቡት፣ ድንበር ያስደፈሩት፣ መሬት እየቆረሱ ለባእዳን የሚያከፋፍሉት፣ ሕዝብን በጎሳ የሚያመሰቃቅሉት፣ የንፁኃንን ደም በከንቱ የሚያፈሱት፣ በሰው አገር ጣልቃ ገብተው የኢትዮጵያን ጭቁን ወታደሮች የሚያስፈጁት፣ ሕዝብን በጉልበት ቀፍድደው ለከፋ ድህነት የዳረጉት እርጉሞች ናቸው::

የቴዲ ለቅሶ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለቅሶ ነው:: እሱ ላይ ያነጣጠረው ጥቃት ኢትዮጵያዊነትን ለሚያከብሩና ለኢትዮጵያዊነት ለሚታገሉ ሁሉ የተሰነዘረ አለንጋ ነው:: ሃገሩን ለሚወድ፣ ለሕዝብ መብት ለሚታገል፣ የተያዘውን ጠማማ አቅጣጫ ለማስተካከል ለሚጥር ሁሉ የተወጠነ መቀጣጫ እንደሆነ ልንገነዘበው ይገባናል::

ሕዝብን በእብሪት የናቁ ወሮበሎች ያገራችሁን ብርቅ እንቁዎች ምክንያት እየፈለጉ ብሩህ አእምሯቸውን ሲያደነዝዙ፣ ሲያስቃዩአቸው፣ ተስፋ ሲያስቆርጡዋቸው እያያችሁ ምንም ነገር ለማይሰማችሁ እንክፎች፤

ጥቅም እስካገኝሁ፣ ምቾቴ አስከተጠበቀ፣ ጊዜያዊ ፍላጎቴ አስከረካ ድረስ የሌላው ጥቃት እኔን አይመለከተኝም እያላችሁ ቁም ነገር ሸሽታችሁ በዋዛ በፈዛዛ ጊዜያችሁን የሚረባ ነገር ሳትሰሩበት ለምታባክኑት ሆድ አደሮች፤

እኛ ከተመቸን ሌላው ለራሱ ይወቅበት የሚል የደነዘ አስተሳሰብ ይዛችሁ ስትናናቁ፣ ስትልፈሰፈሱና፣ ስትስገበገቡ ወገኖቻችሁን ከረሃብ፣ ሃገራችሁን ከኋላ ቀርነት፣ ወንድሞቻችሁንና እህቶቻችሁን ከምዝበራ ማላቀቅ ተስኖአችሁ በሕዝብ ስም ለምትነግዱ የፖለቲካ ደላሎች፣

ሕዝብ የሰጣችሁን ሃላፊነትና ትዕግስት የተሞላበት እድል መጠቀም አቅቷችሁ፣ ቂም በቀልና እብሪት ወጥረዋችሁ ሃገርን የተሻለ ደረጃ ማድረስ በሚገባችሁ ጊዜ አሁንም የልመና ማሰሮአችሁን እየያዛችሁ ነጭ ልመና የምትልመጠመጡት አገር አጥፊዎችና ወሮበሎች፤

ቴዲስ ከዕድሜው በላይ የድርሻውን ተወጥቷል፣ ወደፊትም ይወጣል!!! በአካል ብታስሩትም እናንተ መቼም ሊኖራችሁ የማይችል የመንፈስ አርካታ አለውና ነፃ ነው:: እንባውም በከንቱ ፈሶ አይቀርም::

የናንተ ሕሊና ግን ምናለበት ጊዜው ሳያልፍበት ከታሰረበት የጨለማ ጉድጓድ ተፈቶ ለሃገር፣ ለወገን፣ እንዲሁም ለሰው ልጅ ደህንነት ቅን ነገር ለመሥራት ቢተጋ ???